የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፷፰
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 68
ADDIS ABABA–24th June, 2003


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፫፻፵፰/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ዓለም አቀፍ ውዝግቦችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የወጣውን ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ....... ገጽ ፪ሺ፪፻፳፮


CONTENTS


Proclamation No. 348/2003

Ratification of the Convention for the Pacific Settlement of International Disputes (1899) Proclamation ....................................... Page 2226


### አዋጅ ቁጥር ፫፻፵፰/፲፱፻፺፭
### ዓለም አቀፍ ውዝግቦችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የወጣውን ኮንቬንሽን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ዋና ዋና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ማቋቋሚያ ሰነዶችን ያፀደቀ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ መንግሥት ዓለም አቀፋዊ ውዝግቦችን በሙሉ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ያለውን ጽኑ አቋም በተደጋጋሚ የገለፀ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ዓለም አቀፍ ውዝግቦችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የወጣውን ኮንቬንሽን ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ዓለም አቀፍ ውዝግቦችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የወጣውን ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፵፰/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION NO. 348/2003
### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR RATIFICATION OF THE CONVENTION FOR THE PACIFIC SETTLEMENT OF INTERNATIONAL DISPUTES

WHEREAS, the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is Party to Instruments Establishing the main International Organizations;

WHEREAS, the Government of Ethiopia has consistently expressed its commitment to the peaceful resolution of all international disputes;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has accepted the Ratification of the Convention for the Pacific Settlement of International Disputes at its session held on 24th day of June, 2003;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows,

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Ratification of the Convention for the Pacific Settlement of International Disputes (1899) Proclamation No. 348/2003,"


ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ትርጓሜ</u>

"ማጽደቅ" ፀንቶ የሚገኝ ዓለም አቀፍ ውልን መቀበልን ይጨምራል ።

፫· <u>ኮንቬንሽኑን ስለማጽደቅ</u>

እ·ኤ·አ· ጁላይ ፳፱ ቀን ፲፰፻፺፱ በሔግ የፀደቀን ዓለም አቀፍ ውዝግቦችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የወጣውን ኮንቬንሽን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት በዚህ አዋጅ አጽድቋል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

"Ratification" includes accession to the convention.

3. *Ratification of the Convention*

The convention for the Pacific Settlement of International Disputes adopted at the Hague on 29th July, 1899, is hereby ratified by the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of 24th day of June, 2003.

Done at Addis Ababa, this 24th day of June, 2003.

GIRMA WOLDEGIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE